መስከረም 22

[illegible] ፪/97

# የኢህአዴግን ጦር ጠማሽ አቋም ላለማገዝ... ሰላማዊውን የፖለቲካ ትግል አለማፍዘዝ

ዛሬ በሃገራችን በአንድ በኩል ጸረ ህዝብና ጦር ጠማሽ ኃይሎች በሌላ በኩል ደግሞ የሰላምና የዲሞክራሲ አማራጭ የሚያቀርቡ ኃይሎች ተፋጠው ይገኛሉ:: ማን ጦር ጠማሽ ማን ሰላም ወዳድ እንደሆነም ግልጽ ይመስለናል::

የኢህአዴግ አመራር "እንኳን በሺህ የሚቆጠሩ የሸምቅ ተዋጊዎች ድፍን ኢትዮጵያ ብረት ቢያነሳብኝ በአሸናፊነት እወጣለሁ" በሚል የቀሸተ ዓለም ውስጥ የሚዋሽቅ ልቡ ያበጠ አጥፊ ኃይል ነው:: በዚያው ልክ ደግሞ ሰላማዊ የፖለቲካን ትግል ከጦር የሚፈራ፣ የውይይትን ጥሪ ከጦር ከተት አዋጅ መለየት የማይችል፣ ውይይትና ድርድር አጉል ጊዜ ማጥፋት የሚመስለው እጅግ ኋላ ቀርና የፖለቲካ ድንኩች የተጠራቀሙበት አመራር ነው::

የኢህአዴግ አመራር ካለበት የፖለቲካ ክስረት የተነሳ በኢትዮጵያ ህዝቦችም ፊት ሆነ በዓለም አቀፍ ደጋፊዎቹ ፊት ከሃገራችን ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች የፖለቲካ ትግል የሚፈልግም የሚችልም ኃይል አይደለም:: ግልጽና ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ አንስቶ አዲስ አበባ ሰልፍ ከሚወጣበት 1000 ዜጋ ይልቅ በሃገራችን ገጠሮች መቶ ሺ ጦር ገጥሞት በሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች [redacted] እርስ በእርስ የሚተላለቁበትን ግጭት ይበልጥ የሚመኝ አመራር ነው:: ሌላውን ሁሉ የትግል ስልት ትቶ እንዲህ ዓይነቱን እልቂት መጋበዙ እንደማንኛውም በህዝብ እምነት የሌለው ኃይል ሌላ የትግል አማራጭ ስለማይታየው ነው

በሃገራችን ዲሞክራቶች ሰፈር ያለው ስእል ግን ከዚህ ጨርሶ የተለየ ስእል ነው ከኢህአዴግ በተቃራኒ የሃገራችን የሰላምና የዲሞክራሲ ኃይሎች የማያጠራጥር የህዝብ ድጋፍና ማንም የማይከደው የፖለቲካ የበላይነት አላቸው:: ይህንን የበላይነት እንዳይነጠቁ እስከሰሩና እስካንከባከቡት ድረስ የትግል ስልት ምርጫቸው ከአሸዋ የበዛ ነው::

ኢህአዴግ የሰላማዊ ፖለቲካ ትግልን በር ለመዝጋት በሚያደርገው ሙከራ የተነሳ እሳትን በእሳት ብለው እሱው በመረጠው የትግል ስልት የሚፋለሙት ታጠቂዎች ይኖራሉ:: ግፍና ጭቆና እየተበራከተ ሲሄድ አንድ ህብረተሰብ እንዳለ ዘላለሙን እጁን ይሰጣል ብለን ስለማናምን እንዲህ ዓይነት ግጭቶች እየተበራከቱ እንደሚሄዱ መጠራጠር አይቻልም:: ግን ደግሞ የሃገራችን የሰላምና የዲሞክራሲ ኃይሎች ይህንን አጥፊ ኃይል እሱው ያዋጣናል ብሎ በህብረተሰቡ ላይ በጫነው የትግል ስልት ብቻ አይገጥሙትም:: ህገ መንግሥቱን ተቀብለው እሱ ደነገገ የተባለውን መብት አንቀጽ በአንቀጽ እየጠቀሱ የኢህአዴግን መንግሥት በገዛ ህጉ ለመፋለም የሚመርጡ ኃይሎች አሉ:: ህገ መንግሥቱን በይዘቱም ሆነ በአጸዳደቁ ሂደት ተቃውመው በሰላማዊና ህጋዊ ዘዴ የሚታገሉ ዜጎች አሉ:: ለዚሁ ዓላማም ሰላማዊና የሀቡእ የትግል ስልት መርጠው በዚያም በኩል ለመሠማራት የሚገደዱ ኃይሎች አሉ:: ባጭሩ የትግል ስልት ምርጫ የማይኖረው ጸረ ህዝቡ ኃይል ብቻ ነው::

ለዚህ ነው በአርእስታችን ኢህአዴግ ወጥመድ ውስጥ ላለመግባትና ጦር ጠማሽ አቋሙን ላለማገዝ የሰላሙን የፖለቲካ ትግል አለማፍዘዝ ያልነው:: በእኛ እምነት እነኢህአዴግ ይህንን የትግል ስልት የጥቂት ህልመኞች ቀሸት አርገው ሊያቀርቡት ቢሞክሩም፣ እንዳይስፋፋና እንዳያጥለቀልቃቸው በሚወስዷቸው የጭቆና ርምጃዎች የተነሳ የሚከፈለው መስዋእትነት እየተበራከተ ቢሄድም ሰላማዊው የፖለቲካ ትግል የሃገራችን የወደፊት እድል ሲወሰን ወሳኝ አስተዋጽኦ ሊኖረው የሚችል የትግል ስልት ነው::

በዚህ ከራስ ጸጉር የበዙ የፖለቲካ፣ የስሻል፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍትህ ችግሮች በሚጨፍሩበት ህብረተሰባችን ይህ የፖለቲካና የዲፕሎማቲክ ትግል መስክ ተሟጦ አልቋል፣ በሩ ሁሉ ተዘግቷል በሚል ሰበብ [redacted] እንዲፈዝ ከተደረገ [redacted]

ዛሬ በትጥቅም ሆነ በሰላማዊው ትግል መስክ ይህ መስዋእትነት እየተከፈለ ነው:: የዚህን መስዋእትነት እድሜ ማሳጠርም ሆነ ፍሬያማነት ለማረጋገጥ የሚቻለው በአንድ ዘዴ ብቻ ነው:: ተቃዋሚ ኃይሎች የዛሬ አራት ዓመት በጋራ ይዘውት የነበረውን የፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ አጥቂነት እንደገና በጋራ ለመጎናጸፍ የሚችሉበትን ዘዴ መሻት አለባቸው:: ለዚህ መንደርደሪያ የሚሆን ባለፈው ዝግጅታችን የጠቀምነው የፖሪሱ 7 ድርጅቶች የተስማሙበት በኋላም የአዲስ አበባው ጉባኤ የተቀበለው አታጋይ ሰነድ አለ::በዚህ ሰነድ መንደርደሪያነት በድርጅቶች መሃከል በተለይ ደግሞ በየድርጅቶቹ አባላት መሃከል ውይይት እንዲካሄድ፣ ከዚያም አልፎ የትግሉ አንድነት ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ ዜጎች በሙሉ እንዲመረምሩት ከሚቀጥለው ዝግጅታችን ጀምረን ለአድማጮቻችን እናቀርባለን::